# የትግራይ ክልል ህዝባዊ ኮንፈረንስ

# የአቋም መግለጫ

መጋቢት 22 ቀን 2010 ዓ.ም

መቐለ

## 1. መግብያ

ከመላ የትግራይ አከባቢዎች በህዝቡ የተወከለው ህዝብ የተሳተበበትና ከኩሉ የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የታደሙበት እና ከመጋቢት 19 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ለአራት ተከታታይ ቀናት በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በቐለ ከተማ ኮንፈረንሳችን ለሰላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲ በሚል መሪ ቃል ሲካሄድ የቆየው ህዝባዊ ኮንፈረንስ በድል ተጠናቀዋል፡፡

የትግራይ ህዝብ እንደ ሌሎች የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሁሉ በፀረ ህዝብ፣ በፀረዴሞክራሲና በፀረልማት ስርዓቶች ለዓፈናና ድህነት ተጋልጦ ረጅም የመከራ ዘመን ያሳለፈ ህዝብ ነው፡፡ከዚህ ብሄራዊ ጭቆናና መደባዊ ብዝበዛ የተነሳም ብሄራዊ ማንነቱ ተነፍጎ፣ ሰብአዊና ዴሞክራስያዊ መብቱ ተከልክሎ በከፋ ድህነትና ኋላቀርነት ሲማቅቅ የነበረ ህዝብ ነው፡፡ የዓፈናና የጭቆና ስርዓቱን ከጫንቃው አሽቀንጥሮ ለመጣል በተለያየ ወቅት ሲያካሂደው የቆየው እንቅስቃሴ በተደራጀ አኳኋን ወደ ትጥቅ ትግል ተሸጋግሮ ለዴሞክራሲና ዴሞክራስያዊ አንድነት በከፍተኛ ፅናትና ብርታት ታግሏል፡፡

ከመላ የኢትዮጵያ ህዝቦችና ዴሞክራስያውያን ኃይሎች ጋር በመሆን የትጥቅ ትግሉን አስተባብሮ ህዝባዊ አላማን ታጥቆ፣ ብቁ የአመራር አቅምና ፅናት በመፍጠር የድህነት ሁነኛ ዘበኛ የነበረውን ፋሽሽታዊ የደርግ ስርዓትና መሰል የትምክህትና የጥበት ኃይሎች ዳግም ላይመለሱ ግብአተ መሬታቸው እንዲፈፀም አድርጓል፡፡ወደር የለሽ የትግል ፅናት በማንገብና ለማመኑ የሚያዳግት ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈልም ድል ተቀዳጅተዋል፡፡ በአገራችን አዲስ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲመሰረትም የራሱን የማይተካ ሚና ተወጥቷል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች በመሪ ድርጅታቸው በኢህአዴግ እየተመሩ ባስመዘገቡት ከፍተኛ ድል የትግራይ ህዝብም ከሌሎች ወንድምና እህትህዝቦች ጋር እኩልነቱን ተረጋግጦ መድሎና ሌሎች የጭቆና መሳሪያዎች በሙሉ ተወግደውለት ፍትሃዊ የሆነ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም የሚያረጋግጥለት ዴሞክራሲያዊ ስርአት መስርቷል፡፡

በውጤቱም ትናንት የድህነትና የኋላቀርነት ተምሳሌት ተደርጋ ትታይ የነበረችው አገርና ክልል ከሌሎ ችብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦችጋር በመሆን ባደረገው እልህ አስጨራሽ ትግልና እንቅስቃሴ እነሆ ዛሬ የፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት፣የዴሞክራሲ ስርአትግንባታና የዘላቂ ሰላም ተምሳሌት ሃገርና ክልል እየገነባ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ በመሪድርጅታችን የተጀመረው የልማት፣ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታና ዘላቂ ሰላም የማረጋገጥ ጉዳይ በታለመለት አኳኋንና ፍጥነት እንዳይራመድ ተግዳሮቶች አጋጥመውታል፡፡ድርጅታችን ህወሓትም በአሁኑ ወቅት ያጋጠሙት ፈተናዎች በሚገባ በመገምገምና በመተንተን እንዲሁም ሁነኛ የመፍትሔ አቅጣጫዎችንና መንገዶችን አንጥሮ በማውጣት ዛሬም እንደ ትናንቱ ውስጡን በዝርዝር በማየት ተሃድሶ መድረክ ገብቶ ራሱን እያደሰ ይገኛል፡፡ የተሃድሶ እንቅስቃሴው በውስጠ ድርጅት ብቻ ታጥሮ መቅረት

የለበትም በማለትም ንቅናቄው ወደ መላው የትግራይ ህዝብና የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች እያሸጋገረው ይገኛል፡፡

ህዝባዊ ትግላችን በየትግል ምእራፉ በርካታ እንቅፋቶች እየተሻገረና በየጊዜው ያጋጠሙት ፈተናዎችንም በብቃት እየመከተ በድል ጎደና እየገሰገሰ እዚህ የለውጥ ምዕራፍ ላይ ደርሰዋል፡፡የሚያጋጥሙን ፈተናዎች ከቀላል እስከ ውስበስብ የየሆኑ የውስጥና የውጭ እንቅፋቶች ያጣመረ ችግር እንደነበረ ይታወቃል፡፡ አሁንምአለ፡፡ ድርጅታችን እንዲህ አይነቱ የተቆላለፈ ችግር ሲያጋጥመው ፣ለውጭ ኃይሎች አቤቱታ እያቀረበና እጅ እየነሳ ለመፍታት የሞከረበት አካሄድ አንድም አልነበረም፡፡ የትግራይ ህዝብ በጭቆና የማቀቀና በሁሉም ዓይነት መለክያ የተጎሳቆለ ህዝብ እንደነበር ድርጅታችን ህወሓት የሚያውቀው እንታ ነበር፡፡ሆኖም የሁሉም ችግሮች መፍትሄ ራሱ የተጨቆነውና ድሃው ህዝብ እንጂ ሌላ የውጭ ኃይል እንዳልሆነ ህወሓት አንድም ቀን ቢሆን ዘንግቶት አያውቅም፡፡ ከህዝቡ ጋር ኣብሮ እየተሰቃየ፣ ከህዝቡ ጋር የተገኘውን ነገር በጋራ እየተካፈለ የሚካፈሉት ከሌለም ከህዝቡ ጋር ኣብሮ እየተራበ ፣ ከህዝቡ ጋር በመሆን ሁሉም የህዝብ ችግሮችና መሰናክሎች በድል አጠናቆአሁን ከሚንገኝበት መድረክ ላይ ደርሷል፡፡

የህዝብ ውግንና የሌላቸው ኃይሎች ችግር ሲያጋጥማቸው ሊፈታልን ይችላል ወደሚሉት ጌታ ሲሯሯጡ ይስተዋላል፡፡ ህዝብ ችግር ፈጣሪ አድርገው መመልከት እንጂ ችግር ፈቺ ነው ብለው ለማመን የሚያስችል ተፈጥሮም ዓላማም እንደሌላቸው የትግራይ ህዝብም ይሁን የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንቅቆ የሚያውቀውና የሚረዳው ነው፡፡ የድርጅታችን ጌታና ወሳኝ ሃይል ግን ህዝብና ህዝብ ብቻ ነው፡፡ ችግርና እንቅፋት ሲያጋጥም መፍትሄ ለማግኘት በቅድሚያ የሚሄደው ወደ ህዝቡ ነው፡፡ ለህዝብ በሚገባ በማስረዳትና መፍትሄዎችን በማስቀመጥ የህዝብ ምክርና ሃሳብ በማዳመጥ፣ በህዝብ ተሳትፎና ወሳኝነት ተንቀሳቅሶ ችግርን በድል እያለፈ የመጣ ህዝባዊ ድርጅት ነው ህወሓት፡፡

ይህ “ኮንፈረንሳችን ለሰላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲ” በሚል መሪ ቃል ታጅቦ ለ4 ቀናት ሲካሄድ የቆየው ህዝባዊ ኮንፈረንስ ቀደም ሲል ያስቀመጥነ ውመሰረታዊ እውነታ በሚገባ የሚያሳይና ድርጅታችን በህዝቡ ላይ ያለው ፅኑ እምነት በግልፅ የሚያረጋግ ጥነው፡፡ እኛከ2000 በላይ መላ የትግራይ አከባቢ ህዝባችን ወክለን የመጣን፣ በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች የምንኖር ቁጥራችን 100 የሚደርስ የትግራይ ተወላጆች እንዲሁም ከሁሉም የሃገራችን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ተወክለን የተሳተፍን 400 ተሳታፊዎች፣ የሃይማኖት መሪዎችና ሌሎች ተጋባዥ እንግዶች እንዲሁም የብዙሃንና የሙያ ማህበራት ተወካዮችን ጨምሮ በአጠቃይ ከ2500 በላይ ተወካዮች የተሳተፍንበት ህዝባዊ ኮንፈረንስ ነው፡፡በአሁኑ

ወቅት እያጋጠመን ያለው ችግር መነሻው በሚገባ ተረድተን፣ መፍትሄዎቹ በጥልቀት በመለየት መላ የሀገሪቱ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ያለንን ዴሞክራሲያዊ አንድነት አጠናክረን የምንወጣበት ልዩና ታሪካዊ ኮንፈረን አካሂደናል፡፡

ይህ በክልል ይሁን በሃገር ደረጃ አጋጥሞ ያለውን ችግር ስር ነቀል በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል አብነታዊ የሆነ ድርጅት በቀጣይነት በማጠናከር ለተልእኮው ብቁ የሆ ነየመንግስት መዋቅር በመፍጠር እና የህዝብ ሁሉን አቀፍ የተደራጀ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር እንደሆነ መላው የትግራይ ህዝብና ወንድም ህዝቦች በሚገባ የምናምንበትና በውል የምንረዳው እውነ ታነው፡፡ ስለዚህም ከመጋቢት19 እስከ 22 ቀን 2010 ዓ.ም ለአራት ተከታታይ ቀናት ሲካሄድ በቆየው ኮንፈረንሳችን የተወያየንባቸው ርእሰ ጉዳዮችና የተደረሱ ድምዳሜዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 2. ኮንፈረንሱ የተወያየባቸው ጉዳዮች

ለአራት ቀናት ያካሄድነው ኮንፈረንስ ያተኮረባቸው ቁልፍ አጀንዳዎች የመሪ ድርጅታችን ህወሓት/ኢህአዴግ ግምገማ መሰረት ያደረገ የሃገራችን ወቅታዊ ሁኔታ፣የውስጠ ድርጅት ሁኔታና የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎች አፈፃፀም፣ የትግራይ ህዝብ አስተዋፅኦ፣ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ፣ ልማትና መልካም አስተዳደርና ቀጣይ አቅጣጫዎች የሚሉ አራት መሰረታዊ አጀንዳዎች ላይ ሰፊግምገማና ውይይት በማድረግ የሚከተለው ባለ15 ነጥብ የአቋም መግለጫ አዘጋጅተናል፡፡

1. ከትግራይ ህዝብ የተላለፈላቸውን ጥሪ አክብረው ከሁሉም የሃገራችን አቅጣጫዎች ይህንን ኮንፈረንስ ለመሳተፍ እዚህ በመካከላችን የተገኙ የሁሉም ብሔሮችና ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተወካዮች ላደረጉት የላቀ ተሳትፎና ላበረከቱት ገንቢ ሃሳብ፣ ለትግራይ ህዝብ ይጠቅሙታል ብለው ያነስዋቸው ጥያቄዎችና አስተያየቶች ከልብ ማመስገን እንወዳለን፡፡ ከሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የተወከሉ ተሳታፊዎች ከሰጡት ገንቢ ሃሳብ በመነሳት የሃገራችን ህዝቦች ህይወት እና ልማት በጋራ መተጋገዝ እናመረዳዳት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እና ለዚህም በጋራ መስራት እንደሚገባም አረጋግጠዋል፡፡ በቀጣይም ቢሆን ሃገራዊ ጥቅማችን እና አንድነታችን አጠናክረን እንደምንቀጥል እያረጋገጥን ዴሞክራሲያዊ አንድነታችን ለማጨናገፍ ላይታች ለሚሉ ፀረህዝብ ሃይሎች በጋራ እንደምንታገላቸውም ቃል እንገባለን፡፡

2. የትግራይ ህዝብና መሪ ድርጅታችን ህወሓት ያካሄዱት እልህ አስጨራሽ ትግልና ከፍተኛ መስዋእትነት አዲሲቷ ፌደራላዊት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ በመገንባት ረገድ የተጫወቱት ሚና መተክያ የለውም፡፡ እኛ በዚህ ኮንፈረንስ የተሳተፍን የሁሉም የሃገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተወካዮች የትግራይ ህዝብና ህወሓት ይህንን አዲስ ስርዓት በመገንባት የነበራቸው አስተዋፅኦ ታሪክ የማይረሳው የኢትዮጵያ ህዝብ ቀዋሚ ሐወልት መሆኑ እናሰምርበታለን፡፡ የትግራይ ህዝብ አሁንም ከሌሎች የሃገራችን ህዝቦች ጋር በመሆን ዋስትና ያለው ሰላም ፣ፈጣንና ፍትሃዊልማት፣ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታና መልካም አስተዳደር በማረጋገጥ የሃገራችን ህዳሴ እውን ለማድረግ በሚደረገው ርብርብ ፅኑ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መከታ ሆኖ እንደሚቀጥል አንጠራጠርም፡፡

3. ባለፉት 27 ዓመታት በሃገር ደረጃ የተመዘገቡ የሰላምና የዴሞክራሲ ድሎች የሁሉም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ጥቅም ያረጋገጡ ናቸው፡፡ይሁን እንጂ ከባለፉት ሶስት ዓመታት ጀምሮ ይህ በከፍተኛ መስዋእትነትና ትግል ያገኘነው ሰላም የሚበጠብጡና፣ ፌዴራላዊ ስርአታችንንም ለአደጋ የሚጋልጡ ሁኔታዎች ገጥመውናል፡፡ እኛ የዚህ ኮንፈረንስ ተሳታፊዎችም ለነዛ ሰላማችንን የሚነሱን አካላት አጥብቀን እየተቃወምንና በፅናት እንደምንታገላቸውም እያረጋገጥን ዋስትና ያለው ሰላማችን ወደ ቦታው ለመመለስ በሚደረገው ርብርብ የሚጠበቅብንን ሁሉን አቀፍ ትግል ለማካሄድ ቁርጠኛ መሆናችንን እናረጋግጥለን፡፡

4. የሃገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለብዙ መዋእል እና ትውልድ በደም፣በ ታሪክ፣ በባህል፣ በእምነት፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ሰንሰለት የተጣመርንና የተሳሰርን ነን፡፡በደስታም ይሁን በሐዘን ጊዜና ሁኔታ በፍቅርና በመተጋገዝ የተገነባ አንድነታችን ቀደም ሲል የነበሩ አፋኝ ስርአታት ጭምር ሊበጥሱት አልተቻላቸውም፡፡ አሁን ደግሞ አንድነታችንና አብሮነታችን ሕገመንግስታዊ መሰረት ይዞ በእኩልነት፣ መከባበር፣ በጋራፍላጎቶቻችንና ጥቅም ላይ የታነፀ አንድነታችን በበለጠ ለማጠናከርና ያለን ብቸኛ አማራጭም ተባብሮ መልማት ወይ ተባብሮ መጥፋት እንደሆነ በማመን ሰላማችን የሚያደፈርስ ማኛውም ዓይነት አስተሳሰብና ተግባርና በፅናገት በመታል ዴሞክራስያዊ ስርአታችንን በአንድነት ለመጠበቅ ያለን ቁርጠኝነት ላቅ ያለ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

5. የትግራይ ህዝብና የህወሓት የበላይነት አለ በሚል በውስጥም በውጭ ማህበራዊ ሚድያዎችና በሌሎች የፅንፈኛ ዲያስፖራ መገናኛ ብዙሃ የሚሰራጨው ወሬ የተሳሳተና ነጭ ውሸት እንደሆነ

ኢህአዴግ ባደረገው ግምገማ የተረጋገጠ ነው፡፡እኛ የዚህ ኮንፈረንስ ተሳታፊዎችም በተመሳሳይ መልኩ በትግራይ ህዝብ እና በህወሓት ላይ የሚቀርቡ ውንጀላዎች ትክክል እንዳልሆኑ በዓይናችን አይተን ያረጋገጥነው ስለሆነ የኢህአዴግ ግምገማና ውሳኔ ትክክል እንደሆነ ደግመን እናረጋግጣለን፡፡የዚሁ አጀንዳ መነሻና መዳረሻ የዚሁ እንቆቁልሽ ባለቤቶች አንድነታችን የማይፈልጉ የጥፋት ሃይሎች የፈጠሩት አሉቧልታ፣ በዚሁ የጥፋት አጀንዳዎቻቸው የእርስ በእርስ መጠፋፋት እንዲኖር ሆን ብለው ያዘጋጁት ሴራ እንደሆነም በውል እንረዳለን፡፡ ይህ እንቆቁልሽ በማናፈስና በማስፋፋት ላይ የተጠመዱ አካላት ዋነኛ ዓላማቸው የትግራይ ህዝብና መሪ ድርጅቱ ህወሓትን ነጥሎ በመምታት፣ በህዝቦች መካከል ክፍተት በመፍጠር ህዝቡና መሪድርጅቱ ከኢትዮጵያ ህዝቦች ለይቶ በማጥቃት አዲስ ተስፋ የሰነቀን ህዝብና ሃገር በከፍተኛ ደረጃ ለማፈራረስ ያለመ ነው፡፡ ስለዚህም ሁሉም የኢህአዴግ እህትና አጋርድር ጅርቶች ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ስርአታችን ለማንኛውም ብሄር በተለየ መልኩ ማዳላትና የተለየ ጥቅም እንደማይፈቅድና በዚህ ዙርያ የሚነሳ መሰረተቢስ አጀንዳ መሆኑን ተረድተው እንዲመክቱት ጥሪያችንን እያቀረብን የትግራይ ህዝብና የህወሓት የበላይነትና ያልተገባ ጥቅም ያገኛሉ የሚል የጠላት አጀንዳ እንጂ የህዙ ስላልሆነ መላ የሃገራችን ህዝቦች በፅናት እንደምንታገለው ልናረጋግጥእን ወዳለን፡፡

6. በልማት ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚታዩ ችግሮች ዋነኛ ምንጫቸው ኋላቀርነትና ድህነታችን መሆኑ አጥብቀን የምንረዳውና የምናምንበት ጉዳይ ነው፡፡ይህ ኋላቀርነታችንና ድህነታችን ምንጭ የሆነው ጠላታችን ዛሬም እንደ ትናንቱ በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መስመራችን የፈጠረልን ፀጋዎችን ተጠቅመን፣እ ስከአሁን ያረጋገጥነው የህዳሴ ሂደት በማስጠበቅና የቀሩንን በማሟላት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ድል በማድረግ፣ በወጣት ልጆቻችን ያለው የማብቃትና የተጠቃሚነት ጉድለት በወሳኝ መልኩ የወላጆችና የህዝብ ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ ተረድተን የበኩላችንን አስተዋፅኦ እንዲኖረን፣ በሴት እህቶቻችን ላይ የሚደርስ ማናቸውም ዓይነት ጥቃት ለመከለከልና በዚሁም የትራንስፎርሜሽን ዕቅዶቻችን በብቃት ለማሳካት እንደሚገባን አምነን፣ በገጠር የክረም ትምርታማነትን የሚጨምሩ የአቅርቦትና ቴክኖሎጂዎችን በመልካም ፍላጎቶቻችን አሟልተን በመጠቀም፣ በከተማም ዕድገት ተኮር በሆኑ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ስራዎቻችን በተደራጀ የህዝብ ንቅናቄ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት በሚደረገው ትግል የመሪነት አስተዋፅኦአችንን ለማበርከት ቃልእንገባለን፡፡

7. በፌዴራላዊ ስርአታችን፣ ሕገ መንግስታችን በተለይም ከአብራካችን የተወጣውና የመጨረሻው የፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአታችን መከታና አለኝታ የሆነውን የሃገራችን የፀጥታ/መከላከያ ሓይል ህዝባዊነቱ በተመለከተ እኛ ብቻ ሳንሆን መላው የዓለም ህዝብ የመሰከረለት ሆኖ ሳለ በትምክህትና ጠባብ ሃይሎች እየደረሰበት ያለው የስም ማጉደፍ ዘመቻና ጥቃት መሰረታዊ ዓለማው፣ ስርአት ማፍረስ መሆኑን በፅኑ እንገነዘባለን፡፡ በመከላከያ ሃይላችን ላይ የሚካሄድ ማናቸውም የስም ማጥፋት ዘመቻና አሉቧልታም አጥብቀን እንቃወማለን፡፡
8. የዜጎች መብት ከዜጎች ግዴታ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም፡፡ የዜጎች መብት የሚከበረው የሌሎች መብት እስካልነካና እስካልደፈረ ድረስ ነው፡፡ዴሞክራሲና አመፅም አብረው አይሄዱም፡፡አንዱ የሌላው ፀር ነውና፡፡ ህዝብና መንግስትም የዜጎችን መብት የሚደፍር ማናኛውም ዓይነት ተግባር በምንም ዓይነት መልኩ ለድርድር የሚያቀርቡት ጉዳይ መሆን የለበትም፡፡ የዜጎች ህይወት እንዳይጠፋ፣ የዜጎችና የመንግስት ንብረት እንዳይወድም አስፈላጊውን ትግልና መስዋእትነት በመክፈል ለመጠበቅ ያለንን ዝግጁነት ከፍተኛመሆኑን እንገልፃለን፡፡በዚህ ረገድ የኢፌዴሪ መንግስት ሰላማችንን ለማስጠበቅ አልሞ ላወጣው አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያለንን ድጋፍ እየገለፅን ለተፈፃምነቱ እንደምንረባረብም ቃል እንገባለን፡፡
9. ሕገመንግስታችን ማንኛውም ዜጋ በመረጠው የሃገሪቱ አከባቢ የመንቀሳቀስ፣ የመኖርና ሃብት የማፍራት ዋስትና ሰጥቷል፡፡ መንግስትም ይህ ህገ መንግስታዊ መብትና ነፃነት በመጣስ በዜጎች ህይወትና ንብረት ላይ አደጋ በሚያደርስ ማንኛውም አካል ይሁን ግለሰብ ወይም የተደራጀ ሃይል ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምት እንዲወስድበት ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡
10. በሃገር ደረጃ ኢህአዴግና የኢፌዴሪ መንግስት፣ በክልል ደረጃ ደግሞ ብሄራዊ ድርጅቶችና ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት ለህዝቦች ጥያቄ በሚችሉት ዓቅም ፈጣን ምላሽ እንዲሰጡ፣ የወጣቶቻችን ችግር የቤተሰብ፣ የመላው ህዝብና በአጠቃላይ የተተኪው ትወልድ ችግር መሆኑን በመገንዘብ የተለየ ትኩረት እንዲሰጡት ጥሪያችንን እያቀረብን፣ ቃል መግባት በሚመለከትም ሊተገበር የሚችልና የህዝብ ጥያቄ በሚገባ የሚመልሰውን ለይቶ ቃል መግባት፣ የማይቻል ከሆነም ከህዝብ ጋር በግልፅ በመመካከር እንደማይቻል እና ለምን እንደማይቻል መግባባት ላይ እንዲደረስበት፣ አጉል ተስፋ መስጠት ግን ህዝብ በድርጅትና በመንግስት ላይ ያለው እምነት የሚያሳጣ በመሆኑ ይህ አካሄድ መዝጋት እንደሚገባ ድርጅቶቻችንና መንግስታችንን ማሳሰብ እንፈልጋለን፡፡
11. የተሃድሶ እንቅስቃስያችን በፍጥነት በመጨረስ ወደ ተግባር መግባት አለብን፡፡ በዚህ የተግባር እንቅስቃሴ ህዝብ ባለቤት ሆኖ ድርሻውን በአገባቡ እንዲወጣ እና ሁሉም በየደረጃው ፍትሃዊ ተጠቃሚእንዲሆን እንሰራለን፡፡ ስለዚህ በድርጅት መሪነትና በመንግስት አስፈፃሚነት የተደራጀ ሁሉን አቀፍ የህዝብ ተሳታፊነት

በሰላም፣ ልማት፣ዴሞክራሲና መልካምአስተዳደር ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት በሚደረግ ርብርብ የሚጠበቅብንን ሁሉ እንደምንፈፅም ቃል እንገባለን፡

12. በፀረ-ዴሞክራሲ፣ በመልካም አስተዳደርና ፍትህ እጦት፣ በኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስና ላይ የሚደረግ ትግል በድርጅት የውስጥ ዝግ መድረክ ታጥሮ የሚቀር መሆን የለበትም፡፡ በድርጅት አጥር የሚወሰን ከሆነ ውጤት አይኖረውም፡፡ የግልፅነትና ተጠያቂነት መርህ በሚያረጋገጥ ፣ህዝብ ባለቤትአድርጎ የሚያሳትፍ አሰራር ዘርግቶ መተግበር እንደሚገባም እናምናለን፡፡ ህዝብም የተጀመረው የተሃደሶ እንቅስቃሴ ለማሳካት ትግሉ እንዲያጠነክርና ከሁሉም ኋላቀርነት ዓይነቶች በፀዳ አኳኋን የመስመሩን ጥራት ለማረጋገጥ የሚጠበቅበትን ሁሉ እንዲያደርግ ጥሪያችንን እቀረብን የዚህ ኮንፈረንስ ተሳታፊዎችም የበኩላችንን የመሪነት ድርሻችን ለመወጣት ዝግጁ መሆናችንን እናረጋግጠለን፡፡

13. በኢህአዴግ እህትና አጋር ድርጅቶች መካከል የሚስተዋለው ማናቸውም ዓይነት መጠራጠር በማያዳግም ሁኔታ በመፍታት የድርጅቶቹ ዴሞክራሲያዊ አንድነትና ህብረት ተረጋግጦ የጋራ ብቁ አመራርነት የሚረጋገጥበት ሁኔታ ካልተፈጠረ በቀር ጉዳቱ የህዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት እስከ መፈታተን የሚደርስ በመሆኑ ድርጅቶች በፍጥነት አንድነታቸውን  እንዲያረጋግጡ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡በዚህ በኩል የሚታይ ችግር የአመራር አንጂ የህዝቡ እንዳልሆነም በትልቁ ልናሰምርበት እንፈልጋለን፡፡ በዚህ በኩል ሁሉም እህት ድርጅቶች በመርህ ላይ የተመሰረተዴሞክራስያዊ አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ እንደ ህዝብ ተደራጅተን በምናደርገው ትግልም ድርሻችን እንደምንወጣም ማረጋገጥ እንፈልጋልን፡፡

14. ብሄር ላይ ያነጣጠረ ጥቃት በማናቸውም መንገድ ተቀባይነት የሌለውና የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች አንድነትና ወንድማማችነት አደጋ ላይ የሚጥር እኩይ ተግባር ነው፡፡ ይህ እኩይ ተግባር ለማንኛውም ብሄር የማይወክል የትምክህተኞችና የጠባብ ኃይሎች አፍራሽ አስተሳሰብና ተግባር መሆኑንም አንዳች ጥርጥር የለብንም፡፡ ከዚህ ተነስተን አንድነታችንና አጋርነታችንን ለማደፍረስ ላይ ታች በሚሉ አካላት ላይ በተባበረ ክንዳችን እንደምንፋለማቸው በጋር እናረጋግጣለን፡፡

15. ይህ ዓይነቱ የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ህዝባዊ ኮንፈረንስ ሁሉም ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ህዝቦች እርስ በርሳችንን የበለጠ እንድንተዋወቅና በችግሮቻችንና ድሎቻችን ዙሪያ አብረን እንድንመካከር በዚህም አንድነታችንን ለማጠናከር ሰፊ እድል የሚፈጥርልን በመሆኑ በህወሓትና በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ለተጀመረው አብነታዊ ተግባር አድናቆታችንና ድጋፋችንን እየገለፅን መሰልለ መድረኮች የህዝቦች አንድነትና ተሳትፎ ለማጠናከር ጠቀሜታቸው ከፍያለ በመሆኑ በፌዴራልና በሁሉምክልላዊ መንግስታት ተመሳሳይ መድረኮች  እንዲዘጋልንጁ ጥሪያችን እናቀርባለን፡፡

**ዘለአለማ ዊክብር ለትግሉ ሰማእታት!**

**ህዝብ ያመነ ያሸንፉል!**

**መጋቢት 22 ቀን 010ዓ.ም**

**መቐለ**